ኢሰመጉ ለ11ኛ ጊዜ የተሰጠውን ዓለም አቀፍ ሽልማት ተሸላሚ ሆነ፤

ሰኔ 03/ 2014ዓ/ም

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) እጅግ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ላደረገው አስተዋፅኦ እ.ኤ.አ በሜይ 30/2022 ከጀርመን አምነስቲ ኢንተርናሽናል በየሁለት ዓመቱ የሚሰጠውን ሽልማት ተሸልሟል።

ኢሰመጉ ከ 1984 ዓ/ም ጀምሮ ለ 30 ዓመታት በኢትዮጵያ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲጎለብት እና የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ አስተምሯል፣ የውትወታ ስራዎችን እየሰራ ቆይቷል፤ የመንግስት አካላት የሚያደርሱትን የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ሲያጋልጥና እርምት እንዲደረግ ሲያሳስብ ቆይቷል።

ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና አተገባበር የመከታተል፣ የመመርመር፣ ለሚመለከታቸው ሁሉ ይፋ የማድረግ እና የመሰነድ ስራን በዋናነት በመስራት ጥሰት የፈፀሙ አካላት በህግ እንዲጠየቁ፣ ተጎጂዎች እንዲካሱ፣ ጥሰቶች እንዳይደገሙ ውትወታ ሲያደርግ፣ ላለፉት ሶስት አስር አመታት ዘልቋል።

ሽልማቱ በእነዚህ ረዥም እና ፈታኝ አመታት ለኢሰመጉ ዓላማ መሳካት አባላቱ፣ በየደረጃው ያሉ የኢሰመጉ አመራር አካላት፣ በየጊዜው ያገለገሉ የኢሰመጉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ በተለያዩ ወቅቶች ድርጅታችንን የመሩ የማኔጅመንት/ አስተዳደር አባላትና ሠራተኞች ያበረከቱት የትግል ውጤት ነው። በዚህ የትግል እንቅስቃሴ አመራሮቹ እና አባላቱ ግድያ፣ እስር፣ ወከባ እና ዛቻ ተፈጽሞባቸዋል። አንዳንዶች ከደረሰባቸው መከራ እና ስቃይ የተነሳ ወደ ባዕድ ሀገር ለመሰደድ ተገደዋል።

ይህ ሽልማት ለበለጠ ስራ የሚያነሳሳን ሲሆን፤ መታሰቢያነቱም ለፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም እና በወቅቱ አብረዋቸው ኢሰመጉን ለመሰረቱት በሙሉ እንዲሁም ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የህይወት ዋጋ ጭምር ለከፈሉ ሁሉ ነው!!!

ሁሉም የሰብዓዊ መብቶች ለሁሉም!!!